ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር ያቸንፋል!

**የሠልፍ ድጋፍ መልዕክት ከአሲምባ ድረ ገጽ አዘጋጆች**

በዘሬው ዕለት (መጋቢት ፲፯ ቀን ፪፻፬ ዓ.ም. – March 26, 2012) በሰሜን አሚሪካ በኒውዮርክ ከተማና በዋሺንግተን ዲሲ የወያኔዎች መንግሥት በልማት ሰበብ ታሪካዊውን የዋልድባ ገዳምን ለማጥፋት እያደረገ ያለውን አስከፊ ሀገር አጥፊ ተግባር ተቃውማችሁ ለተሠላፋችሁ ኢትዮጵያውያን ሀገር ወዳዶች፣ ምዕመናን በሙሉ የአሲምባ ድረ-ገጽ አዘጋጆች ( http://www.assimba.org/ ) በምታደርጉት ትግል ከጎናችሁ የምንቆም መሆናችንን እያስታወቅን የዚህን ሠልፍ ዘገባ በመላው ዓለም ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን መልዕክቱ በአስቸኳይ እንዲተላለፍ እንደምናደርግ ቃል እንገባለን።

> *"First they came for the communists, and I didn't speak out because I wasn't a communist. Then they came for the trade unionists, and I didn't speak out because I wasn't a trade unionist. Then they came for the Jews, and I didn't speak out because I wasn't a Jew. Then they came for me and there was no one left to speak out for me."    is a famous statement attributed to pastor Martin Niemöller (1892–1984) about the inactivity of German intellectuals following the Nazi rise to power and the purging of their chosen targets.*
>
> *ከዚህ በላይ ያለው የማርቲን ነሞለር የእንግሊዝኛ ጥቅስ በጀርመን የነሂትለር ናዚዎች በሥልጣን ላይ ሳሉ ያደረሱትን ሰለባ የተማረውና ቀድሞ የነቃው ክፍል እኔን አይመለከተኝም በማለት በዝምታ ያሳለፈበትን ሁናታ የሚገልጽ ጽሁፍ ሲተረጎም እንዲህ ይላል፦*
>
> *"በመጀመሪያ ኮሚኒስቶችን ማሳደድ ጀመሩ፥ ኮሚኒስት አልነበርኩምና ዝም አልኩ። ቀጥለውም የሠራተኛ ማህበራት አባላትን ማሳደድ ጀመሩ፣ የሠራተኛ ማሕበር አባል አልነበርኩምና ምንም አልተናገርኩም። ከዚያም ይሁዶችን ማሳደድ ጀበሩ፣ ይሁዳ አልነበርኩምና ምንም አልተነፈስኩም። ከዚያ እኔኑ ማሳደድ ሲጀምሩ ሊጮኽልኝ የሚችለው ሁሉ አልቆ ነበርና ለኔ የሚናገር ማንም አልነበረም"*

*ከዚህ በላይ ያለው ጽሑፍ ምልዕክት ላለፈው ሃያ ዓመታት ወያኔዎች በመካከላችን መተማመን እንዲጠፋ ሕዝቡን እያናከሱ ኢትዮጵያዊነትን በፈቀዳቸው መልክ ሲያፈራርሱ፣ ኢትዮጵያን ገምሰው ወደብ አልባ ሲያደርጉ፣ እህቶቻችንን፤ ልጆቻችንን ለመካከለኛው ምሥራቅ ዘማናዊ ባርነት ሲቸረችሩ፣ የኢትዮጵያን ለም መሬት ለዓለም ቱጃሮች በልማት ስም ሲያድሉ፣ በኃይማኖታችን ጣልቃ ሲገቡ*

አባቶቻችን እንዳስተማሩን ቀፎው እንደ ተመታ ንብ በአንድነት ብድግ አለማለታችንን አያመላክትምን? በየተራ እየተመታን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ከማጣታችን በፊት ባገኘነው መልክ ሁሉ እየተሰባሰብን እንምከር፣ እንኮምስስ፣ የችግራችን መሠረት ወያኔዎችና መሰሎቻቸው ናቸውና እምቢኝ እንበል። ለዚህም ከዚህ ጽሁፍ ጋር አያይዘን ያወጣናቸው ወገኖቻችን ፍርድ አልባ በወያኔ እሥር ቤት ደብዛቸው እንዲጠፋ ሲደረግ ለመሆኑ ስንቶቻችን ልንጮኽላቸው ፈቃደኞች ነኝ? ወይስ ኢሕአፓዎች ናቸውና አያገበንም እንበል? የቀይ ሽብር ተዋንያን ለፍርድ ቀርበው ዛሬ ዛሬ በምሕረት በተለቀቁባት ኢትዮጵያ ወያኔዎች እኒህን ወገኖች ለፍርድስ እንዴት ሊያቀርቧቸው አልቻሉም? ከላይ ያቀረብነው ጥቅስ መልዕክቱ ጥልቅ ነው። ስንቶቻችንስ ገብቶናል? ስንቶቻችንስ ከዚህ ጽሁፍ ጋር ያያዝነውን ምስል በዚህች ደቂቃ ከፍ በማድረግ ዝምታችንን ልንሰብር ቆርጠናል? የወያኔን ኢትዮጵያን የማውደም ዘመቻ ለመቋቋም ቆርጦ መነሳትን ይጠይቃል። ዛሬ ባንቆርጥ ለመቁረጥ እናስብበት።

የአሲምባ ድረ-ገጽ ( [http://www.assimba.org/](http://www.assimba.org/) ) ላለፉት ፯ ዓመታት ድምጻቸው ለተነፈገ ወገኖቻችን ሁሉ ድምጽ ሆኖአል። በጸረ-ኢትዮጵያዊነት አባዜ የተለከፉ ፖለቲከኞች የሚነዙብንን የሥነልቡና ዘመቻ የሚቋቋሙ የተለያዩ መልዕክቶችን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ከማቅረብ ወደ ኋላ አላልንም። ወደፊትም እንዲሁ። ለምሳሌ በዛሬው ዕለት ይህንን ድረ-ገጽ ቢጎበኙ፦

1. በዋልድባ የመንፈስ አባት የሆኑት ከመንግሥት  ጋር ያደረጉትን ውይይትና እየደፈሰባቸው ያለውን ሁናቴ በዓለም ላሉ ኢትዮጵያውያን ያቀረቡት አቤቱታ በፍኖተ-ነብረት ራዲዮ ከአዳርቃይ ያደረጉትን ቃለ መጠይቅ መስማት ይቻላል።
2. በሌባኖስ በኢትዮጵያ ኤምባሲ ፊት ለፊት እየተደበደበች በመኪና ውስጥ ስትከተት የሚያሳየው ቪዲዮ በኋላም ራሷን ገድላለች የተባለችው ዓለም ደቻሳ ሊመለከቱ ይችላሉ
3. [Ethiopian Social Assistance Committee (ESAC)](#)  እዚሁ ኒው ዮርክ ያለ ድርጅት በቅርቡ በየአረብ ሀገሩ ለሚንገላቱ ወገኖቻችን ድምጽ ለመሆን የሚያደርጉትን ጥረት የሚያመለክት ዘገባ በማንበብ እናቶች፣እህቶችና ልጆቻችን እንዴት መሳተፍ እንደምንችል የቀረበ ዘገባ ማንበብ ትችላላችሁ።
4. የኢትዮጵያ የፖለቲካ እሥረኞች አንድነት ኮሚቴ ካለምንም አድልኦ ለሁሉም ወገኖች በዓለም መድረክ ሁሉ የሚያደርገውን ጩኸት በተከታታይ መግለጫዎችና እንቅስቃሴዎች መከታተል ይችላሉ።
5. በቅርቡ ወ/ሮ ገነት ግርማ በተባበሩት መንግሥታት በኖርዌይ ከ400 በላይ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ካለ ፈቃዳቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ የተደረገበትን ሁኔታና በሩቅ ምሥራቅ በኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ እየደረሰ ስላለው ወከባ ያቀረቡትን የንግግር ቪዲዮ ሊመለከቱ ይችላሉ።
6. በኢሳት ቴሌቪዥን ቃለ መጠይቅ ተደርጎላቸው የነበሩት የአባ ኒቆዲሞስ ምስክርነት፣ (አነጎች በሀረር በአማሮች ላይ አድርሰውት ስለነበረው ዕልቂት) ባልታወቀ ምክንያት እንዳይታይ የታገደው በድረ-ገጾችን ላይ ይታያል።

ከዚህም በላይ ይህ ድረ-ገጽ የተመሠረተበት ዋና ምክንያት በቀይ ሽብር ሰለባ የሆኑ ወገኖቻችንን ስምና ታሪክ የሚዘረዝር ልዮ ገጽ አብጅቶ በዓለም ዙሪያ ካሉ ወገኖች ከሚደርሱን መልዕክቶች

ያሰባሰብናቸውን መመልከት ይችላሉ። ከሁሉም በላይ እርስዎም ሊያካፍሉን የሚችሉትን እንዲለግሡን በማክበር እንጠይቃለን። በአጠቃላይ ይህ ድረ-ገጽ ሌላው (አብዛኛው) የማይዳስሰውን፤ ከሁሉም በላይ በኢትዮጵያዊነት ላይ ጠንካራ አቋም ያለው ነጻ ድረ ገጽ ነው። ዕምነታችን ለሁሉም እኩል የምትሆን፣ ሁሉም ዜጋ ተከባብሮ የሚኖርባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እንዴት እንመሥርት ለሚለው ጥያቄ መልስ መስጠት ነው። ከክልል ፖለቲካ ዴሞክራሲያዊነት አለመገኘቱን ያለፉት ሃያ ዓመታት በቂ ትምህርት ሰጥተውናል። ኢትዮጵያ የተመሠረተችው በዓለም ያሉት ሀገሮች ሁሉ በተመሠረቱበት አኳያ ነው ብለን እናምናለን። ስለሆነም ወደ ኋላ በመመልከት ኢትዮጵያን እንደ አዲስ በሬፈራንደም እንደገና እንመሠርታለን የሚለውን የሌሎቹን ወያኔዎች ፍልስፍና አንጋራም!

ኢትዮጵያዊነት ያለጥርጥር በትግላችን ያቸንፋል!

እምቢኝ ለወያኔዎች! እምቢኝ ለዘር ፖለቲከኞች

የአሲምባ ድረ-ገጽ ዝግጅት ክፍል።




Aberash